# የኮቪድ-19 ክትባቶች፡- በአስራዎቹ እድሜዎች ያሉ ማወቅ ያለባቸው ነገሮች

## ጽሁፍ

በአካል ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ ጓጉተዋል? ተለይተዉ በመቀመጥዎ ምክንያት ስፖርቶች ወይም ሌሎች ተግባራት እንዳይቋረጡ ይፈልጋሉ? ከቤተሰብ ወይ ጓደኞች ጋር መዝናናት መቻል ይፈልጋሉ? የኮቪድ-19 ክትባቶች ወደእነዚህ ሁሉ ነገሮች መመለሻ መንገድ ናቸው።

ለወጣቶች እና ወላጆቻቸው ከመከተባቸው በፊት ጥያቄዎች መጠየቃቸው የተለመደ ነው። ጥያቄ ካልዎት፣ ዶክተር ይጠይቁ። የተወሰኑ ፈጣን መረጃዎችን እነሆ፡-

- የኮቪድ-19 ክትባቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ ነው።
- ለአዋቂዎች ጥናት እንደተደረገባቸዉ ሁሉ፣ እድሜያቸው በአስራዎቹ ቤት ላሉትም ጥናት ተደርጎባቸዋል፣ ስለዚህ እንደሚሰሩ እና ደህንነታቸው እንደተጠበቀ እናውቃለን።
- የኮቪድ-19 ክትባት ነጻ ነው እንዲሁም ID ማሳየት የለብዎትም።
- የኮቪድ-19 ክትባቶች መካንነትን አያስከትሉም።

ማንም ሰዉ መርፌ መወጋትን አይወድም፣ ነገር ግን ዘና እንዲሉ የሚረዱዎት ነገሮች አሉ።

- በጆሮ ማዳመጫ የእርስዎን ተወዳጅ ሙዚቃ ያዳምጡ።
- በዝግታ፣ በጥልቀት ይተንፍሱ።
- ከሚያግዝዎት ሰው ጋር የአይን ግንኙነት ያድርጉ።
- የተለጠፈ ማስታወቂያ ጥቃቅን ጽሁፎችን ለማንበብ መሞከር የመሳሰሉ፣ ክፍል ውስጥ ያለ ነገር ላይ ማተኮር።
- ራስዎን ያዘናጉ፣ የእግርዎን አውራ ጣት ለማንቀሳቀስ ይሞክሩ።

ክትባት ከወሰዱ በኋላ ለአንድ ቀን ወይም ከዚያ በላይ ጤንነት ላይሰማዎት ይችላል፣ ነገር ግን ብዙ ጊዜ መለስተኛ ነው። እናም፣ በኮቪድ-19 በመታመምዎ ወይም በኮቪድ-19 ለተያዘ ሰው በመጋለጥዎ ኳራንቲን ማድረግ በማስፈለጉ ምክንያት ለቀናት ወይም ለሳምንታት ከትምህርት ቤት ወይም ከሌሎች ተግባራት ውጪ ከመሆን በጣም ይሻላል።

ያስታውሱ፣ ከ 18 በታች ከሆኑ ለመከተብ የወላጅ ወይም የአሳዳጊ ፍቃድ ያስፈልጋል። ወላጅዎ ወይም አሳዳጊዎ ከእርስዎ ጋር መሄድ ካልቻለ፣ ወደ ክሊኒኩ ደውለው ስለ ፍቃድ ሂደታቸው ይጠይቁ።

የኮቪድ-19 ክትባትን የሚያገኙባቸው ብዙ ቦታዎች አሉ። ከ 18 አመት በታች ለሆኑ ሰዎች ሁሉም የ ኮቪድ-19 ክትባቶች አይገኙም፣ ስለዚህ መሄድ የሚፈልጉበት ቦታ ማግኘት የሚችሉት ክትባት እንዳለው እርግጠኛ ለመሆን ያረጋግጡ። www.vaccines.gov ላይ በአቅራቢያዎ ያሉ ቦታዎችን መፈለግ እና በክትባት አይነቶች መለየት ይችላሉ።

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-4989
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

8/11/21 (Amharic)

*ይህን መረጃ በተለየ ቅርጸት ለማግኘት፣ ለሚከተለው ይደውሉ፡- 651-201-4989።*